የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ነሀሴ ፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21[st] Year No.66
ADDIS ABABA 14[th] August, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯ ዓ.ም

የደሕንነተ ሕይወት (ማሻሻያ) አዋጅ.........ገጽ ፹፫፻፰

CONTENTS

Proclamation No.896/2015

Biosafety (Amendment) Proclamation...Page 8308

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯

## የደሕንነተ ሕይወት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ስለደሕንነተ ሕይወት የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፷፻፶፭/፪ሺ፩ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የደሕንነተ ሕይወት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፮/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ማሻሻያ**

የደሕንነተ ሕይወት አዋጅ ቁጥር ፷፻፶፭/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጾች (፩)፣ (፬)፣ (፮)፣ (፱)፣ (፲፪)፣ (፲፯) እና (፲፰) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፩)፣ (፬)፣ (፲፪)፣ (፲፯) እና (፲፰) ተተክተዋል:-

"፩/ 'ልውጥ ህያው' ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል

## PROCLAMATION No. 896/2015

## A PROCLAMATION TO AMEND THE BIOSAFETY PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Biosafety Proclamation No. 655/2009;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Biosafety (Amendment) Proclamation No.896 /2015".

2. **Amendment**

The Biosafety Proclamation No. 655/2009 is hereby amended as follows:

1/ Sub-articles (1), (4), (6), (9), (12), (17) and (18) of Article 2 are deleted and replaced by the following new sub-articles (1), (4), (6), (9), (12), (17) and (18):

"1/ 'modified organism' means any biological entity which has been artificially synthesized, or in which the genetic material or the expression of any of its traits has been changed by the

ስለተከተተበት የዘረመሎች ይዘት ወይም የባህሪው ክስተት የተለወጠበት ህያው ነው፤

፬/ 'ዝግ አጠቃቀም' ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ የሚከተል ያልታቀደ ተጽዕኖን ለመከላከል በቁሳዊና በንጥረ ነገራዊ ከለላ ታጥረውና በሚኒስቴሩ በወጣው በተገቢው መመሪያ በተፈቀደው ስፋት ባልበለጠ ቦታ ተወስነው ልውጥ ህያውን እንዲሰሩ፣ እንዲወገዱ ወይም ትምህርትንና ምርምርን ጨምሮ እስከ መስክ ምርምር ሙከራ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል፤

፮/ 'ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት' ማለት ለዝግ አጠቃቀም ሳይሆን በአገር ውስጥ ወደ አካባቢ ለመልቀቅ በአንድ ልውጥ ሕያው ላይ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ከሚኒስቴሩ የሚሰጥ የአዎንታ ጽሑፍ ነው፤

፱/ 'ጠንቅ' ማለት በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ሂደት ሲታይ በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ ወይም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ ከልውጥ ሕያዋን ተፅዕኖ በመመንጨቱ በብዝሐ ሕይወት ጥበቃና ዘላቂ ጠቃሚነት በተለይም በብዝሐ ሕይወት እሴት፣ በአገር በቀል የዕውቀት ሥርዓትና በአካባቢያዊ ማህበረሰቦች ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ነው፤

፲፪/ 'ሚኒስቴር' ወይም 'ሚኒስትር' ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአካባቢና የደን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

introduction of any foreign gene whether taken from another organism, from a fossil organism or artificially synthesized;

4/ 'contained use' means any operation up to field trial in which modified organisms are produced ,destroyed or used in some other way including for teaching and research isolated by physical and chemical barriers in space not exceeding the requirement stated in the appropriate directive issued by the Ministry with a view to effectively preventing their contact with, and their unintended impact on ,human, animal and the external environment;

6/ 'advance informed agreement' means a written consent granted by the Ministry for the undertaking of any transaction of modified organism destined to release into the environment in the country other than for contained use;

9/ 'risk' means short, medium or long-term danger that may befall on human or animal health, biological diversity, the environment or socio-economic conditions arising from the impact of modified organism on the conservation and sustainable use of biological diversity, especially with regard to the value of biological diversity, indigenous knowledge systems and local communities;

12/ 'Ministry' or 'Minister' means the Ministry or Minister of Environment and Forest ,respectively;

፲፯/'አመልካች' ማለት የሚጠይቀውን እንቅስቃሴ ለማካሄድ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ወይም ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ያመለከተ ሰው ነው፤

፲፰/ 'ፈቃድ የተሰጠው ሰው' ማለት ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ወይም ልዩ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ የተሰጠው ሰው ነው፤"

፪/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፱)፣ (፳)፣ (፳፩) እና (፳፪) ተጨምረው ነባር ንዑስ አንቀጾች (፲፱) እና (፳) ንዑስ አንቀጾች (፳፫) እና (፳፬) ሆነው ተሸጋሽገዋል:-

፲፱/ 'ዘመናዊ ጥበበ ሕይወት' ማለት፡-

ሀ) በመርፌ በመውጋት ኑክለይክ አሲድን ወደ ሕዋስ በቀጥታ መክተትን ጨምሮ በቤተ ሙከራ እንዲካሄድ የዲኦክሲራይቦኑክለይክ አሲድን የማቀናጀት ሥራን በማካሄድ፣

ለ) ከስነ ስያሜ አኳያ ሲታይ ከአንድ ፋሚሊ ውጪ የተገኙ ሕዋሳትን ወደ አንድ ሕዋስነት በማቀላቀል፣

ተፈጥሯዊ ፊዚዮሎጂካዊና የመዳቀል መከላከያዎችን አስዘልሎ ከባህላዊ የማዳቀል ሂደቶች ውጪ የሚደረግ አዲስ ዝርያን የማዳቀልና የመምረጥ ተግባር ነው፤

፳/ 'ልዩ ፈቃድ' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ልውጥ ሕያውን ወደ አካባቢ መልቀቅን ሳይጨምር በዝግ አጠቃቀም ለምርምር ወይም ለትምህርት ለማዋል ልውጥ ሕያውን ወደ አገር ለማስገባት ከሚኒስቴሩ በጽሁፍ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

17/ 'applicant' means any person who submits an application to the Ministry seeking an advance informed agreement or a special permit to engage in a transaction;

18/ 'authorized' person' means a person who has been given an advance informed agreement or a special permit by the Ministry to engage in a transaction;"

2/ sub-articles (19), (20), (21) and (22) are added after sub-article (18) of Article 2 of the Proclamation and the existing sub-articles (19) and (20) are re-numbered as sub-articles (23) and (24):

"19/ 'modern biotechnology' means the application of:

a) In vitro nucleic acid techniques, including recombinant deoxyribonuclic acid and direct injection of nucleic acid into cells or organelles;

b) fusion of cells beyond the taxonomic family;

that overcome natural physiological, reproductive or recombination barriers and that are not techniques used in traditional breeding and selection;

20/ 'special permit' means a written permit granted by the Ministry for importation of a modified organism for contained use in research or teaching but not for release into the environment in accordance with this Proclamation;

፳፩/ 'የውጭ ላኪ' ማለት ልውጥ ሕያውን ከውጭ አገር ሆኖ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚልክ ሰው ነው፤"

፫/ በአዋጁ በማናቸውም ሥፍራ "ባለሥልጣን" የሚለው ስያሜ ተሠርዞ "ሚኒስቴር" በሚለው ተተክቷል፤

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፬ ተተክቷል:-

"፬.**<u>የአዋጁ ዓላማ</u>**

የአዋጁ ዓላማ፡-

፩/በሰውና በእንስሳት ጤና፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ፣ በማህበረሰቦችና በአጠቃላዩ በአገር ላይ ከልውጥ ሕያዋን ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ማስቀረት ወይም ቢያንስ እስከ ኢምንታዊነት ደረጃ ድረስ ማሳነስ፤ እና

፪/ ዘመናዊ ጥበበ ሕይወትን ጨምሮ ለብዝሐ ሕይወት ጥበቃና ዘላቂ አጠቃቀም የሚያገለግል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትንና በቴክኖሎጂ ዝውውር መጠቀምን ማሻሻል፤

ነው።"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል:-

"፭.**<u>ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነትን ከሚኒስቴሩ ሳያገኝ ልውጥ ሕያውን ወደ ክፍት አካባቢ የመልቀቅ እንቅስቃሴን ማካሄድ አይችልም።

21/ 'foreign exporter' means any person under the jurisdiction of another country who exports a modified organism;"

3/ the designation "Authority" appearing anywhere in the Proclamation is deleted and replaced by "Ministry";

4/ Article 4 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 4:

"4. **<u>Objective of the Proclamation</u>**

The objective of the Proclamation shall be to:

1/ protect human and animal health, biological diversity and in general, the environment, local communities and the country at large by preventing or at least managing down the adverse effects of modified organisms to levels of insignificance; and

2/ enhance access to and transfer of technologies, including modern biotechnology, that serve for conservation and sustainable use of biological diversity."

5/ Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 5:

"5. **<u>Advance Informed Agreement</u>**

1/ Without prejudice to the provision of Article 3 of the Proclamation no person may engage in any transaction destined for release of modified organism to the environment without obtaining an advance informed agreement from the Ministry.

፪/ ለውጥ ሕያውን ወደ አካባቢ የመልቀቅ እንቅስቃሴን ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት የተዘጋጀ ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።

፫/ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ለማግኘት ማንኛውም አመልካች በዚህ አዋጅ መሰረት በወጡት ደንቦች እና መመሪያዎችየተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ እስከ አንቀጽ ፳ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፯ እስከ አንቀጽ ፳፩ ሆነው የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተጨምሯል፡-

"፮. **ልዩ ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ሰው ልዩ ፈቃድ ሳይሰጠው የዝግ አጠቃቀም እንቅስቃሴ ሊያካሄድ አይችልም።

፪/ የዝግ አጠቃቀም እንቅስቃሴ ሊያካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

፫/ ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለውጥ ሕያውን ወደ አካባቢ መልቀቅ የለበትም።

፬/ በዝግ አጠቃቀም ምርምር የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ በመውሰድ ከእንቅስቃሴው ሊመጣ የሚችሉትን ጠንቆች በሙሉ ማስወገድ አለበት።"

2/ Any person who intends to engage in any transaction destined for release of modified organism to the environment shall submit to the Ministry an application prepared in accordance with this Proclamation and the regulations and directives issued hereunder.

3/ Any applicant intending to obtain an advance informed agreement shall comply with the requirements set in the regulations and directives issued hereunder."

6/ Articles 6 to 20 of the Proclamation are renumbered as Articles 7 to 21, respectively, and the following new Article 6 is added:

"6. **Special Permit**

1/ No person may engage in any contained use transaction without obtaining a special permit.

2/ Any person who intends to obtain a special permit for contained use transaction shall submit an application to the Ministry in accordance with the regulations and directives issued hereunder.

3/ A person granted a special permit may not release a modified organism into the environment.

4/ Any person who is conducting research in a contained use shall take all necessary measures to completely avoid the risks that may arise from the transaction."

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፡-

"፱. <u>ልውጥ ሕያውን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት</u>

፩/ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ወይም ልዩ ፈቃድ ሳይገኝ ልውጥ ሕያውን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

፪/በዝግ የመጠቀም ፈቃድን ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ልዩ ፈቃድ እንጂ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሊያሰጥ አይችልም።

፫/ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በላኪው አገር ህግ መሰረት እውቅና ያለው መሆን አለበት።

፬/ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጥ ለሚኒስቴሩ የሚቀርብ ማመልከቻ በውጪ ላኪው የተፈረመ የልውጥ ሕያዉን ምንነት ከሚገልፅ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል፡-

"፬/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ለአመልካች ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፡

ሀ) የተጠየቀውን ምርምር ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ተቋሞችና ሥርዓቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ፤

7/ Article 9 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (6) of this Article) is deleted and replaced by the following new Article 9:

"9. <u>**Importation of Modified Organisms**</u>

1/ Importation of any modified organism without obtaining an advance informed agreement or a special permit is prohibited.

2/ An application for contained use is not subject to an advance informed agreement but to a special permit.

3/ A person who applies to the Ministry for an advance informed agreement shall have a recognition as the law of the exporting country authorizes the exporter to take such responsibility.

4/ An application for a special permit for the importation of a modified organism shall be accompanied by a statement signed by the foreign exporter indicating the identity of the modified organism."

8/ sub-article (4) of Article 15 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (6) of this Article) is renumbered as sub-article (5) and the following new sub-article (4) is added:

"4/ The Ministry shall issue special permit to an applicant if:

a) there are facilities and institutional systems required to conduct the specified research as per the regulations and directives issued pursuant to this Proclamation;

ለ) ዝውውሩ ወደ አካባቢ የማይለቀቅ ከሆነ፤

ሐ) አመልካቹ ምርምሩን ለማካሄድ ተፈላጊው ብቃት ያለው ከሆነ፤ እና

መ) ጉዳቱን ለመቀነስ ወይም ወደ ኢምንትነት ለማውረድ የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀ የአሠራር ሥርዓት ያለ ከሆነ።"

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፯ (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፯ ተተክቷል:-

"፲፯. <u>ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነትና ልዩ ፈቃድ ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ</u>

፩/ ልውጥ ሕያው ለንግድ ሥራ ወደ አካባቢ እንዲለቀቅ የተሰጠ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ለአስር ዓመት የፀና ይሆናል።

፪/ ለዝግ አጠቃቀም የተሰጠ ልዩ ፈቃድ ለአምስት ዓመት የፀና ይሆናል።

፫/ በትራንዚት ለማስተላለፍ የተሰጠ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ለሦስት ወር የፀና ይሆናል።

፬/ ለንግድ ሥራ ወደ አካባቢ እንዲለቀቅ የተፈቀደው ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ወይም ለዝግ አጠቃቀም የተሰጠ ልዩ ፈቃድ ሊያከትም አንድ ዓመት ሲቀረው ስምምነቱ ወይም ልዩ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘምለት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሊያመለክት ይችላል።

፭/በትራንዚት ለማስተላለፍ የተሰጠ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ሊያከትም አንድ ወር ሲቀረው ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘምለት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሊያመለክት ይችላል።

b) the transaction is not destined for release to the environment;

c) the applicant has the required qualification to conduct the research; and

d) if standard operating procedures that prevent or minimize risks to the insignificant level are in place."

9/ Article 17 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (6) of this Article) is deleted and replaced by the following new Article 17:

"17.<u>Validity Period of Advance Informed Agreement and Special Permit</u>

1/ An advance informed agreement for commercial release of modified organism shall be valid for ten years.

2/ A special permit for contained use shall be valid for five years.

3/ An advance informed agreement for transit of modified organism shall be valid for three months.

4/ The authorized person may request for extension of the validity period of advance informed agreement for a commercial release or a special permit for contained use of modified organism one year before the expiry date of the validity period.

5/ The authorized person may request for extension of the validity period of advance informed agreement for transit of modified organism one month before the expiry date of the validity period.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ሚኒስቴሩ ከግንዛቤ የመነጨው ስምምነት እንዲራዘም ወይም የጠንቅ ግምገማው እንዲከለስ ወይም በድጋሚ እንዲሠራ ሊወስን ይችላል።"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) ተተክተዋል:-

"፫/ የጉምሩክ ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የታገተውን ልውጥ ሕያው በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ እና በሰው ጤና ላይ የከፋ ጠንቅ በማያስከትል ማከማቻ ቦታ ማስቀመጥ አለበት።

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተጠርጥሮ የታገተውን ዕቃ ናሙና በመፈተሽ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ልውጥ ሕያውን ማካተቱን ወይም አለማካተቱን ማረጋገጥ አለበት።"

፲፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳ (ቁጥሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፪ እና ፳፫ ተጨምረው ነባሮቹ አንቀጾች ፳፩፣ ፳፪ እና ፳፫ እንደ ቅደም ተከተላቸው አንቀፅ ፳፬፣ ፳፭፣ እና ፳፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

"፳፪. <u>ብሄራዊ የደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ</u>

ለሚኒስትሩ ተጠሪ የሆነ እና ደህንነተ ህይወትን በሚመለከት መንግስትን የሚያማክር ብሄራዊ የደህንነተ ህይወት አማካሪ ኮሚቴ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ይቋቋማል።

6/ The Ministry may, upon the receipt of an application pursuant to sub-article (4) of this Article, decide whether to extend the validity period of an advance informed agreement or to order the revision or the doing of the risk assessment."

10/ sub-articles (3) and (4) of Article 21 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (6) of this Article) are deleted and replaced by the following new sub-articles (3) and (4):

"3/ The custom's officer shall store the modified organism impounded pursuant to sub-article (2) of this Article in an appropriate storage facility in such a manner that potential risks to biodiversity, the environment and human health are minimized.

4/ The Ministry shall, by examining the samples within five working days, verify whether the material impounded pursuant to sub-article (2) of this Article contains any modified organism or not."

11/ the following new Article 22 and Article 23 are added after Article 21 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (6) of this Article) and the existing Articles 21, 22 and 23 are re-numbered as Articles 24, 25 and 26 respectively:

"22. **<u>National BioSafety Advisory Committee</u>**

A National Biosafety Advisory Committee, accountable to the Minister shall be established by regulation to be issued by the Council of Ministers.

**፳፫.ስለቅሬታ አቀራረብ**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ስምምነት ወይም ልዩ ፈቃድ ለማግኘት ወይም ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማረዘም የቀረበን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ ወይም ስምምነቱን ወይም ልዩ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሠረዝ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠ በ፵፭ ቀናት ውስጥ በሚኒስቴሩ ለተቋቋመ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታውን ማመልከቻ ሊያቀርብ ያልቻለ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደ በ፲ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ ይችላል።

፫/ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አባላት እና አደረጃጀት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት ይወሰናል።

፬/ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ውጤቱን ከውሳኔ ሃሳብ ጋር በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ያቀርባል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በሚኒስትሩ የተሰጠ ውሳኔን በሚመለከት በሕግ አተረጓጎም ስህተት ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠ በ፷ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።"

**23.Grievance Handling**

1/ Any person aggrieved by the rejection of an application submitted in accordance with this Proclamation for the issuance or extension of the validity period of an advance informed agreement or special permit, or the suspension or revocation of the agreement or the special permit may, within 45 days from the date of such decision, lodge his complaint with the Grievance Hearing Committee established by the Ministry.

2/ Any person who cannot submit his complaint in accordance with sub-article (1) of this Article due to force majeure may submit his application within 10 days after the end of the force majeure.

3/ The grievance handling committee members and their composition shall be determined by the regulations and directives issued pursuant to this Proclamation.

4/ The grievance handling committee shall up on examining the compliant submitted to it pursuant to sub-article (1) of this Article provide its findings and recommendation to the Minister within five working days.

5/ An applicant aggrieved by the decision of the Minister given under sub-article (4) of this Article may, with respect to error of interpretation of law, appeal to the Federal High Court within 60 days from the date of the decision.''

**፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of August, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**